# *ሃሳብ ቃልን ወለደ፤ቃልም ተግባርን*

**አለም /ከጊዮን/**

ኢትዮጵያ በራሷ ጥረትና በልማት አጋሮቿ ድጋፍ ድህነትን በአፋጣኝ እያሸነፈች በእድገት ጎዳና መረማመድ ከመጀመሯም በላይ በፊትም ቢሆን የድህነታችን ምክንያት በወንዞቻችን የመጠቀም መብታችን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በእጅጉ ተገድቦ ቆይቷል፡፡ ይሁንና እድሜ ለታታሪው ህዝባችን ያን ዘመን በአስተማማኝ አኳኋን ተሸግረን ታልቁን የልማት ህልማችንን በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድባችን አማካኝነት እውን የምናደርግበት አዲሱ ዘመን ተበስሯል፡፡ ስለሆነም ከእንግዲህ ወዲያ መብታችንን እንዳንጠቀም የሚያጓትት ምንም ነገር አይኖርም፡፡

በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በአይነቱና በግዙፍነቱ በሃገራችን ቀዳሚውን ስፍራ እንደመያዙ፤ ፋይዳውም እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በረጅም ዘመን ታሪካችን በአባይ ላይ ቀደም ካሉ ዓመታት በፊት ልማት እንዳናካሂድ ዋነኛው ማነቆ ሆኖ የነበረው ለግንባታ የሚያስፈልግ የቴክኒክ፤የገንዘብ ብድርና ድጋፍ ከውጭ እንዳይገኝ ግብጾች በፈጠሩት ተጽእኖ እና ያራምዱት በነበረው ኢ-ፍትሃዊ አመለካከትና በያዙት የግለኝነት አቋም ምክንያት ነበር፡፡ ከዚህም ባለፈና ይከተሉት የነበረው ወታደራዊ የማስፈራራት ስትራቴጂም አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ነበር፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለይም ያለፉት መንግሥታት ብስለት የተላበሰ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ያለማድረግ/አዋጭና አማራጭ ስልት ቀይሶ/ ያለመንቀሳቀስና የቁርጠኝነት ማነስም የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደነበረው በተወሰነ ደረጃ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ዛሬ ግን ይህ ታሪክ ተቀይሮ ሁኔታዎች ሌላ መልክ እየያዙና ተጠቃሚነታችንን የሚያረጋግጥ ይበል የሚያሰኝ ግንቢ እርምጃ በኢትዮጵያ መንግሥት መወሰድ ጀምሯል፡፡ በመሆኑም “የቆየውን ማነቆ ስንሰብር የምናስተላልፈው መልእክት ሌሎች ግድቦችን ሁሉ ከዚህ ያነሱ ናቸውና ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎቱ ብቻ ሳይሆን አቅሙም አለን፡፡” ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ የመሰረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ እንደተናገሩት ፡፡

ለመሆኑ ሀገራችን የተፈጥሮ ሀብቶቿን በተለይም የውሀ ሀብቷን እንዳትጠቀም ያደረጋት ምክንያት ምን ይሆን? ጥያቄው በሁሉም ኢትዮጵያዊ አእምሮ ውስጥ እንደሚመላለስ መገመት አያዳግትም፡፡ በቴክኖሎጂ አለማደጋችን ይሆን? በመስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር? የተነሳሽነት ማነስ? የውጭ ተጽእኖ ወይስ የፖሊሲ ችግር?

ኢትዮጵያ የውሀ ሀብቷን በአግባቡ ለመጠቀም የምታደርገውን ጥረት በበጎ የማይመለከቱ ጎረቤት ሀገሮች መካከል  ግብጽ በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች፡፡
በ1929 ዓ/ም የአባይን ወንዝ አጠቃቀም በተመለከተ በእንግሊዝና ግብጽ መካከል የተፈረመው የስምምነት ሰነድ የራስን ጥቅም ብቻ በማስከበር የሌሎች የተፋሰስ ሃገሮችን የጋራ ተጠቃሚነት ወደ ጎን የተወና ያገለለ ስለነበር ግብጽን በናይል ወንዝ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም የግድብም ሆነ የመስኖ ግንባታዎች እንዲሰሩም ሆነ እንዳይሰሩ ድምጽን በድምጽ የመሻር ብቸኛ ባለመብት ያደረገ ነበር፡፡ በመሆኑም ግብጽ ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ተጠቃሚ እንዳትሆን የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ተጽእኖዎችን ስትፈጥር መቆየቷን እንረዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ታታሪና ለችግር የማይንበረከክ  ቢሆንም ያለፉት ስርአቶች ይከተሉት በነበረው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዎች ለሃገራዊ ህልውናችን ወሳኝ የሆኑትን  ችግሮቻችንን ወደጎን በመተው በውስጣዊ ችግሮቻችን  ላይ ትኩረት ያደረጉና ከውጭ ወደ ውስጥ የመመልከት ሁኔታ በመኖሩ አገራዊ ጥቅሞቻችንና ህልውናችንን በተገቢው ደረጃ ሊያረጋግጡ አልቻሉም፡፡ ሰፊ መሬት፣ ብዙ የሰው ሀይልና  በየአቅጣጫው ከአመት አመት የማይነጥፉ ወንዞች እያሉን የልማት አቅማችንን አሟጠን እንዳንጠቀም መደረጋችን ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች ተብለው ከሚጠቀሱ ሀገሮች ተርታ ቢያሰልፈን ሊገርመን አይገባም፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የውጭ ጉዳይና የሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ብሔራዊ ጥቅማችንን የማስጠበቅና ሃገራዊ ህልውናችንን የማረጋገጥ ተልዕኮ ያለው ሆኖ ተቀርጿል፡፡  ካለፉት ጥቂት አመታት ጀምሮ ልማታዊ መንግስታችን የድህነትን አከርካሪ አጥንት በመስበር ስርነቀል ለውጥ ለማምጣት ልማትና እድገትን የሚያፋጥኑ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ከመንደፍ ጀምሮ  ልማትን ለሚያመጡ ተግባራት ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ በየዘርፉ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ልማታዊ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ለሀገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ አልምተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የሀገሪቷን ኢኮኖሚ እንዲያሳድጉ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፡፡ በተለይም በመንግስት አቅም የሚሰሩ የውሃ ሀብቶቻችንን ጥቅም ላይ ለማዋል ባደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል የነበረውን የሀይል አቅርቦት ችግር በምን ያህል ደረጃ ለመፍታት እንደተቻለ ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት የጀመሩት የግልገል ጊቤ፣ የተከዜና የጣና በለስ ግድቦች አብነቶች ናቸው፡፡

በአሁኑ ሰዓትም የሀገሪቱን የሃይል አቅርቦት ከሶስት እጥፍ በላይ ለማሳደግ በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ ታላቁ የህዳሴ ግድብን ለመገንባት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ግዙፍ የሃይል ማመንጫ ግንባታ ሲጠናቀቅ ከ63 ቢሊዬን ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ እንደሚይዝም ይገመታል፡፡ ግድቡ አሁን ያለውን የጣና ኃይቅ የውሃ መጠን እጥፍ እንደሚይዝና 5ሺ 250 ሜጋ ዋት ኃይል እንደሚያነመነጭ ታውቋል፡፡ ይህ ፕሮጀክት መንግስት በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማገባደጃ ላይ የሃገሪቱን ኃይል የማመንጨት አቅም አስር ሺህ ሜጋ ዋት ለማድረስ የያዘውን ግብ እውን ለማድረግ የሚያስችል ግምባር ቀደሙ ፕሮጀክት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ግድቡ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የሀገራችንን የመስኖ ልማት አጠቃቀም ቴክኖሊጂ በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ከዚህ ተጓድኝ ሃገራዊ ተጠቃሚነት ባሻገርም ሀገራችን ለጎረቤት ሀገሮች በተመጣጣኝ ክፍያ ልታቀርበው በሚያስችላት የኤሌክትሪክ ኃይል የውጭ ምንዛሬዋን በማሳደግ ኢኮኖሚያዊ አቅሟን ይበልጥ ማጎልበት የምትችልበትን አማራጭ ይፈጥርላታል፡፡ የህዳሴ ግድብ ከሚያስገኘው ከነዚህ  በርካታ ሃገራዊና ክፍለ አህጉራዊ ኢኮኖሚያዊና የሕዝብ ለሕዝብ ትብብር ጠቀሜታዎች አንጻር ሲመዘንም አባይ ለእኛ “የጪስ አልባ ነዳጅ” ያህል ዋጋ ያለው ነው፡፡

ለሀገራችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የሚሰጥና የሀገር አለኝታ የሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ስራ ወጪ ከ70 እስከ 80 ቢሊዬን ብር እንደሚፈጅ ተጠቅሷል፡፡ ምንም እንኳ ቀደም ሲል የተደረጉ በርካታ ጥረቶች ስኬታማ ባይሆኑም፣ በቀጣይ ዓለም አቀፍ ትብብሮች ለማግኘት መንግስት ያላሰለሰ ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ከማድረግ ሳይቆጠብ እርዳታና ብድር ቢገኝም ባይገኝም በራሱ አቅም የአባይ ወንዝን ለልማት ለማዋል ተዘጋጅቷል፡፡ ግድቡ መሰራት ካለበት፣ አሁን በተጨባጭ ያለው አማራጭም ይህ ብቻ ነው፡፡ የማይነጥፈው የመንግስት ሀብት ህዝቡ በመሆኑ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ  የአገራችን ዜጎች፣ የግሉ ሴክተርና የልማት አጋሮቻችን ርብርብ ካደረጉ የተፈለገውን ግብ መድረስ እንደሚቻል መንግስት ያምናል፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ግብ በመነሳትም የቦንድ ሽያጭ አዘጋጅቷል፡፡

የመንግሥት ቦንድ መንግሥት ከሕብረተሰቡ ብድር ለማግኘትና ለአበዳሪው ወለድ በመስጠት አበዳሪውን ተጠቃሚ የሚያደርግበት የውል ሰነድ  ሲሆን፣ ፕሮጀክቶችን በረጅም ጊዜ ለመስራት ሲታቀድና ለፕሮግራሙ በተመደበው በጀት ላይ እጥረት በሚያጋጥምበት ጊዜ ከአምስት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ የጊዜ ገደብ በሰነድ ሽያጭ ከህብረተሰቡ

ገንዘብ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መንግስት ፈጣን ልማቱን ለማስቀጠል ያቀረበውን ቦንድ በመግዛት የዜግነት ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡ የነገውን ብሩህ ተስፋ በማሰብ ያለውጭ ብድርና እርዳታ በራሳችን ሀብት ያለንን አሚጠን በመጠቀም ይህን ግዙፍና ታላቅ ግድብ እንዲሁም ድህነታችንን ታሪክ በማድረግ ሃያልነታችንንና አብሮነታችንን በማሳየት ሕያው የታሪክ አሻራ ማኖር የዚህ ትውልድ ታሪካዊ አደራ ሆኖ ከፊት ለፊታችን ቀርቧል፡፡፡፡

ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልምና ባለሀብቱ በገንዘብ፣ ባለሙያው ሙያዊ ግዴታውን በመወጣት ፣ ወጣቱ በጉልበቱ አዛውንቱ በፀሎቱ ሁሉም እንደየአቅሙና ችሎታው ትውልድ የሚሻገር አሻራውን ማሳረፍ ይጠበቅበታል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ አቅሙ በፈቀደው መጠን ርብርብ ቢያደርግ የፕሮጀክቱ ግንባታ የሚፈጀው 80 ቢሊዮን ብር ጌጡ እንጂ ሸክሙ አይሆንም፡፡ የፕሮጀክቱ መሰራት ዞሮ ዞሮ የሚጠቅመው ህዝቡን ራሱን በመሆኑ ዛሬን ሳይሆን ነገን እናስብ፡፡

ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ህብረተሰቡ በግንባታው ዘርፍ ለሚቀርብለት ጥያቄ በሚሰጠው ምላሽ ላይ "" የኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ የትኛው እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ በተለመደው ወኔው ምንም ያህል ድሃ ብንሆንም ድህነታችንን ለማስወገድ ማንኛውም ዓይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነው፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቱ መስራት አለበት እንደሚል ለአፍታም ያህል አልጠራጠርም፡፡ "" በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ያላቸውን ጽኑ እምነትና ኩራት በልበ ሙሉነት ገልጸዋል፡፡ ዎገንም አላሳፈረም ይህ ከተነገረ ማግሥት ጀምሮ ከዳር እስከዳር የድጋፍ ድምጹን በከፍተኛ ሃገራዊ ስሜት በማሰማት ላይ ይገኛል፡፡

ስለ አባይ በተለያዩ ጊዜያት ድምጻውያን አቀንቅነውለታል፡፡ ገጣሚያን በማይነጥፍ ብእራቸው ስንኝ ቋጥረውለታል፡፡ ይሁን እንጂ የአገራችንን ዛፎች ገነዳድሶ ከመሄድ፤አፈሩን ጠራርጎ ለባእድ ሀገራት ከማስረከብ የዘለለ ፋይዳ አልነበረውም፡፡እንደ ግዝፈቱና የማልማት አቅሙም ለዘመናት ሳንጠቀምበት ኖረናል፡፡ "በእጅ የያዙት … " ይባል የለ፡፡ በመሆኑም የአባይን ጥቅም ላይ ማዋል መሰረት በማድረግ ፡-

ማደሪያ ሳይኖረው…… ግንድ ይዞ ይዞራል<br>
የሚባለው ተረት……. ከእንግዲህ ይቀራል<br>
እንዲህ እንደዛሬው….. መልካም ቀን ሲወጣ<br>
ግንድም ይዘህ አትዞር…. ማደሪያም አታጣ፡፡

በማለት አቀንቃኟ እንዳዜመችው ቦንዱ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በየደረጃው እንዲሳተፍበት ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለሽያጭ እንዲውል የተዘጋጀ ሲሆን፤

የገንዘብ አስተዋጽኦ ማበርከት ለሚፈልጉ  በኢትዮጵያ ልማት ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተው ሂሳብ ቁጥር የግንባታውን ፕሮጀክት ማገዝ ይቻላል ፡፡

በሌላ በኩልም ቦንዱን ከመግዛት ጎን ለጎን የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮችና ፕሮግራሞች እንዲካሄዱ አማራጭ ስልቶችን በመንደፍ ግንባታው በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ ሁላችንም የየራሳችንን የቤት ስራ በመውሰድ የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት ስለሚያስችል "" ድር ቢያብር አንበሳ ያስር "" የሚለውን የአበው ብሂል እውን ያደርገዋል፡፡